# የማሽከርከር ስነ-ባህሪ ትምህርት

ማሽከርከር ስነ-ባህሪ ትምህርት ዋና አላማው አሽከርካሪው ችግር የሚያደርስ አደጋ እና ህልፈተ ህይወትን ለመቀነስ ነው፡፡ ይህም በዋናነት ሊከናወን የሚችለው አስፈላጊ አሽከርካሪ ባህሪ ለማስተካከል /ለማሻሻል/ ነው፡፡

**ስነ-ባህሪ፡-** የሁለት የተለያዩ ቃላት ትርጉም ውጤት ሲሆን

> **ስነ፡-** ማለት ሰናይ ከሚለው የግዝ ቃል የተወሰደ ሲሆን መልካም፣ ቆንጆ፣ ውብ፣ ወዘተ የሚል ትርጉም ሲኖረው
>
> **ባህሪ፡-** ማለት የሰው አስተሳሰብ አመለካከት ድርጊት ውጤት ነው ስለዚህ የሁለቱ ቃል ጥምር ትርጉም መልካምና ጥሩ የሆነ የሰው ልጅ አስተሳሰብ እንዲሁም አመለካከት ማጎናጸፍ ማለት ይሆናል፡፡ በተለያ የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች ለስነ-ባህሪ የተለያዩ ትርጓ ሰቱዋል ከነዚህ ትርጓሜዎች ከነዚህ ትርጓሜዎች ውስጥ ሁለቱ እንደሚከተለው ተገልፀዋል፡፡

**ስነ-ባህሪ፡-** ሰዎችና የእንስሳት ባህሪ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና ዲሲፒሊን ነው፡፡

ስነ-ባህሪ፡- ባህሪና የአእምሮን አስተሳሰብ ሂደትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና ዲሲፒሊን ነው ፡፡ ተፈጥሮና አካባቢ ባህሪ ላይ ያላቸው ሚና የሰው ልጅ ባህሪ የወርስ እና የአካባቢ የጋራ ውጤት እንደሆነ የተለያ የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች ይስማማሉ፡፡

## የባህሪ መለዋወጥ መንስኤዎች

የባህሪ መለዋወጥ መንስኤዎች በዋናነት የሚከተሉት ናቸው፡፡ ውርስ/ተፈጥሮ/ አካባቢዋ ሁኔታዎች አካላዊ ሁኔታዎች ሀይለ ስሜታዊ ውጥረት ስልጠና የመሳሰሉት ጉዳዮች ናቸው፡፡

1. የውርስ ባህሪ፡- ከምንላቸው መካከል ችኩልነት ትግስት ማጣት ልታይ ልታይ ባይነት ለነገሮች ያለንን ትኩረት መወነስ የመሳሰሉት ናቸው፡፡
2. አካባቢዋ ባህሪ፡- ከምናላቸው መካከል ህግ ስነ ስርአት አለማክበር ለአደጋ ያለን ግምት ማነስ የመሳሰሉት ናቸው፡፡
3. አካላዊ ሁኔታ፡- በሚደክም እና የህመም ስሜት በሚሰማን ወቅት የባህሪ ለውጥ ልናሳይ እንችላለን፡፡

4. ሃይለ ስሜት፡- ውስጣዊ ፍላጎት ፍቅርን ጥላቻን ሃዘን ወዘተ መግለጽ ሂደትን ይመለከታል፡፡ ለነገሮች ያለንን ስሜት ከሚፈለገው በላይ በሚሆንበት ወቅት ሃይለ ስሜት ውጥረት ይከተለናል፡፡ ይህም ለባህሪ መለወጥ ምክንያት ይሆናል ማለት ነው፡፡
5. ስልጠና፡- በተሽከርካሪው ከሚደርሰው አደጋ የተወሰነው አሽከርካሪዎች ብቃት ማነስ ችግር የሚፈጠረው አደጋ ደረጃውን የጠበቀ የአሽከርካሪዎች ስልጠና ሊወገድ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የስልጠና ባህሪ ለውጥ ማምጫ መንገድ በመሆኑ ነው፡፡

## የስነ-ባህሪ ግቦች

የስነ ባህሪ ግቦች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው

1. ባህሪን መግለጽ
2. የተለያዩ ስነ ባህሪያትን መንስኤ ማብራራት
3. አሁን ያለንን ባህሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት የወደፊቱን መተንበይ
4. ባህሪን ማሻሻል ናቸው
5. የማሽከርከር ስነ-ባህሪ፡- ማለት አሽከርካሪዎች በሚያሽከረክሩበት ወቅት የሚያሳዩትን ባህሪ የሚያጠና የሳይንስ ዘርፍ ነው፡፡

የመልካም አሽከርካሪ ባህሪያት መግለጫዎች

1. ትህትና
2. ርህራሄ
3. ህግንና ደንብን ማክበር
4. ከሌሎች መንገድ ተጠቃሚዎች ጋር መንፈሳዊ ትስስር መፍጠር
5. የሌላን መንገድ ተጠቃሚ ስሜት መጋራት
6. የአንዳንድ ፈጠራ ልምድን ማዳበር

የማሽከርከር ሥነ-ባህሪያዊ ጉዳዮች የምንላቸው

1. ዝግጁነት
2. መነቃቃት
3. መረጃን መሰብሰብና የመተርጎም ሂደት ናቸው

1. ዝግጁነት - ማለት የብስለት የችሎታ የመነሳሳትና የትምህርት የጋራ ውጤት ነው

የዝግጁነት መገለጫዎች

- ከማሽከርከራችን በፊት ጤንነታችንን ማወቅ
- የተሽከርካሪያችን የቴክኒክ ሁኔታ ማየት
- የመንገዱን የትራፊኩን የአየሩን ሁኔታ ማወቅ ናቸው

2. መነቃቃት፡- ባህሪን ወደ ግብ የሚያደርስ ሂደት ነው
3. መረጃን መሰብሰብና የመተርጎም ሂደት በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ እነሱም
   - 3.1 መገንዘብ
   - 3.2 ትኩረት
   - 3.3 ማስተዋል ናቸው

3.1 መገንዘብ፡- መረጃ አካባቢያችን በስሜት ህዋሶቻችን የመቀበል የመለወጥና ወደ አእምሮአችን የመላክ ሂደት ነው፡፡ ማለትም በመስማት በማየት 80-90 በማሽተት በመዳሰስ የአካባቢያችን ሁኔታ የምናውቅበት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ቀይ መብራት የበራ መሆኑን ከስሜት ህዋሳችን ውስጥ በአይናችን በማየት የበራውን ቀይ መብራት ወደ አእምሮ መላክ

3.2 ትኩረት፡- አሽከርካሪዎች ለማሽከርከር የሚረዳቸውን መረጃ በማተኮር በስሜት ህዋሶቻቸው የደረሰውን መረጃ ዋናውን እና ተፈላጊውን የመምረጥ ሂደት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ቀይ የትራፊክ መብራት ቁም የሚል መልእክት የሚያስተላልፍ መልእክት መሆኑን በመረዳት አማራጭ መውሰድ

3.3 ማስተዋል፡- በስሜት ህዋሶቻችን አማካይነት የመጣውን የመምረጥ ማቀናበርና ትርጉም የመስጠት ሂደት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ቀይ የትራፊክ መብራት ቁም የሚል መልእክት የሚያስተላልፍ በመሆኑ ፍሪሲዮንና ፍሬን ሁለቱን በማቀናበር ተሽከርካያችንን እግረኛ ማስተላለፊያ ዜብራውን ሳናልፍ ማቆም ትርጉም ይሆናል ማለት ነው፡፡

## የአሽከርካሪዎች ሙያዊ ሥነ-ምግባር

ሙያ፡- ማለት በህብረተሰቡ ውስጥ የተከበረና የተወደደ የስራ መስክ ሆኖ በተወሰነ እውቀት መስክ በትምህርት በስልጠና የሚገኝ ነው፡፡

ሥ-ምግባር፡- ማለት መልካሙንና መጥፎዎን ለመለየት የሚያስችልና መጥፎውን ትተን መልካሙን እንድንከተል የሚያደርገን ነው፡፡

የሙያ ሥነ-ምግባር፡- ማለት ባለሙያዎች በተሰማሩበት ሙያ የተሰራውን ስራ ውጤታማ እንዲሆን የሚያደርግ የሙያ ምግባር ነው፡፡

አሽከርካሪነት፡- የአእምሮና የአካል እንቅስቃሴ ቅንጅት የሚጠይቅ ሙያ በመሆኑ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል፡፡

ሙያዊ ስነ-ምግባራቸውን አክብረው የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡፡

- ያለምንም ዕረፍት ከ4 ሰዓት በላይ አያሽከረክሩም
- የትራንስፖርት ህግንና ደንብን ያከብራሉ
- ከነዱ አይጠጡም ከጠጡ አይንዱ
- የመኪናውን ጠቅላላ አካል ይጠብቃሉ
- ለእግረኞች ቅድሚያ ይሰጣሉ
- የእንቅልፍ ስሜት በተሰማቸው ጊዜ እረፍት ያደርጋሉ

## የአሽከርካሪዎች አላስፈላጊ ባህሪያት

- ከሚፈለገው በላይ ራስ ወዳድነት
- ሞገደኝነት
- ኃይለ ስሜታዊ አለመረጋጋት
- ቸልተኝነት
- ልታይ ልታይ ባይነት /ትኩረት ለመሳብ መሞከር/
- ኃላፊነትን መዘንጋት
- ሱሰኝነት.....ወዘተ

## በማሽከርከር ችሎታ ላይ የአልኮል መጠጥ ተፅዕኖ

አልኮል መጠጥ በአዕምሮአችን ላይ ያሉትን ነርቮች የሚያደነዝዝ ሲሆን በማተኮር ውሳኔ መስጠትን የአካላዊ ቅልጥፍናን በመቀነስ ለትራፊክ አደጋ መንስኤ ይሆናል፡፡

አልኮል ጠጥተው የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች ባህሪያት የሚከተሉት ናቸው

- በራሱ ረድፍ ውስጥ ያለመቆየት
- በከፍተኛ ፍጥነት ማሽከርከር
- ለመዞር ሰፊ ቦታ መውሰድ
- በጣም ዝግ ባለ ፍጥነት ማሽከርከር

- ያለ አግባብ /በግዴለሽነት/ ምልክት ሳያሳዩ መቅደም

መጠጥ የጠጣ አሽከርካሪ ማድረግ ያለበት

- ሌላ ትራንስፖርት /ታክሲ/ መጠቀም
- የሚያውቀውን ጓደኛ በስልክ ጠርቶ እየነዳ እንዲወስደው ማድረግ
- በጠጡበት ቦታ ማደር
- ከቤተሰብ /ከጓደኛ? ጋር በመሆን ቤት አካባቢ መጠጣት

ሞገደኛ፡- ማለት ለራሱ ብቻ የሚያስብ የሰው ስሜት የማይገባው ተንኮለኛ ሽብር ፈጣሪ ነው፡፡

የሞገደኛ አነዳድ ፈርጆች

የሞገደኛ አነዳድ ፈርጆች በሶስት ይከፈላሉ እነሱም

1. ትዕግስት ማጣትና ትኩረት አለመስጠት
2. ተፅዕኖ የማድረግ ትግል
3. ግድ የለሽነትና የመንገድ ላይ ፀብ ናቸው

## ሶስቱ የማሽከርከር ባህሪያት ዘርፎች

የማሽከርከር ባህሪያት በሶስት ይከፈላሉ እነሱም

ሀ. የስሜት ባህሪ

ለ. የመገንዘብ ባህሪ

ሐ.የክህሎት ባህሪ

ሀ. የስሜት ባህሪ፡- ፍላጎትን አመለካከት እሴትን መነሳሳትን እና ማናቸውንም ግብን ያለመ ድርጊት ያጠቃልላል፡፡

ለ. የመገንዘብ ባህሪ፡- መረዳትን ማሰብን ምክንያትን ውሳኔ መስጠትን እና የሰውን ድርጊት ማጤንን ያካትታል፡፡

ሐ. የክህሎት ባህሪ፡- አስፈላጊ የሚሆነውን በማገናዘብ በአዕምሮ አዛዥነት በአካል ዕንቅስቃሴ የሚፈፀም ማናቸውንም የክህሎት ባህሪ ያካትታል፡፡

## የማሽከርከር ባህሪ ስነ-ባህሪያዊ ዘርፎች

1. ኃላፊነት
2. ጥንቃቄ /ደህንነት/
3. ብቃት /ችሎታ/ ናቸው

## 1. ሀላፊነት

### ሀ. ስሜታዊ ሀላፊነት

- ለሌሎች ማሰብና ስነ-ምግባራዊነት

ምሳሌ፡- በሌሎች ላይ አደጋንና ጉዳትን ላለመፍጠር መጠንቀቅ /መፍራት/

የስሜታዊ ሀላፊነት ጉድለት

- ራስ ወዳድነትና ቅንነት የጎደለው አስተሳሰብ

ለምሳሌ፡- በራስ ላይ የደረሰውን ችግር /እክል/ በሌሎች ላይ እንዲደርስ መሻት

### ለ. አእምሮአዊ ሀላፊነት

- አዎንታዊ ህሊናዊ አስተሳሰብና አእምሮአዊ ጤንነት

ለምሳሌ፡- የራስንና የሌሎችን የማሽከርከር ተግባር ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ቀድሞ መገመት ወይም በህሊና ማሰብ

የአእምሮአዊ ሀላፊነት ጉድለት

- አሉታዊ ህሊናዊ አስተሳሰብና አደገኛ የሆነ ባህርይ
- አደገኛ የሖነ የማሽከርከር

ለምሳሌ፡- ኪና እያሽከረከሩ በቅዠትና በቀን ህልም ውስጥ መዘፈቅ

### ሐ. ክህሎታዊ ሀላፊነት

- ደስተኝነትና እርካታ

ለምሳሌ፡- በማሽከርከር ወቅት ከፍተኛ የሆነ ንቃትና የተረጋጋ መልካም ስሜትን ማዳበር

ክህሎታዊ ሀላፊነት ጉድለት

- ውጥረትና ድብርት

ለምሳሌ፡- በማሽከርከር ሂደት መፍራት፣ መጨነቅ አለመረጋጋት ወ.ዘ.ተ

## 2. ጥንቃቄ /ደህንነት/

### ሀ. ስሜታዊ ደህንነት

- ራስን ማዘጋጀትና ሚዛናዊነት /እኩልነት/

ለምሳሌ፡- ሌሎች የአውራ ጎዳና ተጠቃሚዎች ሊሰሩት የሚችሉትን ስህተት በማሰብ ጥንቃቄና ሰፋ ያለ ግንዛቤ መውሰድ ወ.ዘ.ተ

የስሜታዊ ደህንነት ጉድለት

- የሞገደኝነት ስሜትና በአጋጣሚዎች የመጠቀም ፍላጎት

ለምሳሌ፡- ሌሎች አሽከርካሪዎች ለመቅደም ራስን ውድድር ስሜት ውስጥ ማስገባት

### ለ. አእምሮአዊ ደህንነት

- ሚዛናዊ መለያ ባህርያት

ለምሳሌ፡- በምናሽከረክርበት አካባቢ እየተከናወኑ ያሉትን ክስተቶች ለመረዳት ሁኔታዎችን መተንተን የአእምሮአዊ ደህንነት ጉድለት

- ሚዛናዊነት የጎደለው መለያ ባህርያት

ለምሳሌ፡- የራስን የማሽከርከር ጥፋት ወደ ሌሎች አሽከርካሪዎች ለማሳበብ መሞከር

### ሐ. ክህሎታዊ ደህንነት

- ትህትና የተሞላበት መግባባትና የመረጋጋት ስሜት

ለምሳሌ፡- ከሌላ አሽከርካሪ ጋር በተፈጠረ አለመግባባት የተከሰተን የስሜት ለውጥ /መረበሽሽ ማስወገድና በፍጥነት ወደ መደበኛ ስሜት ለመመለስ መሞከር

የክህሎታዊ ደህንነት ጉድለት

- ትህትና የጎደለው

ለምሳሌ፡- ሌሎች የአውራጎዳና ተጠቃሚዎች በቃል ወይም በምልክት /በአካላዊ/ መሳደብ

### 3. ብቃት /ችሎታ/

**ሀ. ስሜታዊ ብቃት**

- ደንብን ማክበርና ልብ ሙሉነት

ለምሳሌ፡- ለትራፊክ እንቅስቃሴ ደንብና ስርዓትን ራስን ማስገዛት

ስሜታዊ ብቃት ማነስ

ደንብን ስርአትን ያለማክበርና በራስ ያለመተማመን

ለምሳሌ፡- በትራፊክ እንቅስቃሴ ሂደት ታጋሽ ያለመሆን

**ለ. አእምሮአዊ ብቃት**

- እውቀትና ግንዛቤ

ለምሳሌ፡- በማሽከርከር ሂደት ሌሎች አሽከርካሪዎች ራሳችን የሰራናቸው ስህተቶች ልብ ማለትና ማስታወሻ መውሰድ

የአእምሮአዊ ብቃት ማነስ

- በመረጃ ያልተደገፈና የተዛባ አስተሳሰብ

ለምሳሌ፡- መንገዱን በሚፈቅደው የፍጥነት ልክ መሰረት ማሽከርከር መንቀርፈፍ እንደሆነ ማሰብ

**ሐ. ክህሎታዊ ብቃት**

- ትክክለኛ ተግባርና ጠንቃቃነት /ንቁነት/
- ለምሳሌ፡- የአካባቢውን ትራፊክ እንቅስቃሴ /ፍሰት/ በመከተል የፍጥነት ገደብ ሳያልፍ ማሽከርከር

የክህሎታዊ ብቃት ማነስ

- ትክክለኛ ያልሆነ አካሂድና የትኩረት ማጣት

ለምሳሌ፡- ያለበቂ አትኩሮትና በሌላ ሀሳብ ተጠመ፣ዶ ማሽከርከር

## የመልካም አሽርካሪ ባህሪያት የማዳበር ስልት

አሽርካሪዎች እራሱ በራሱ የሚያደርገው ስህተትን የማረም ሂደት አንድ የመልካም አሽከርካሪ ባህሪ ነው፡፡ ይህ ስልታዊ የሆነ እራስን በራስ ስህተትን የማረም ዘዴ የ3ቱ ‹‹መ ዎች›› ራስን የመለወጥ ሂደት ይባላል፡፡

ይህ አሽከርካሪ ዕራሱን በራስ የመለወጥ ሂደት 3 ደረጃዎች አሉት እነሱም

1ኛ ደረጃ፡- አሽከርካሪው እኔ ይህ አሉታዊ ልምድ አለኝ ብሎ ማመን /መጥቀስ/

2ኛ ደረጃ፡- አሽከርካሪው አሉታዊውን በራሱ ላይ መመስከር

3ኛ ደረጃ፡- አሉታዊ ልምዶችን መቀየር ናቸው፡፡

ውጤታማ የመግባባት ክህሎትን ለማዳበር

በሃሳብ መግባባት ለሰው ልጅ የዕርስ በዕርስ ግንኙነት መሰረት ነው፡፡ ይህም የሚደመጥ ክህሎትንና መረዳዳትን ያዳብራል፡፡

ውጤታማ መግባባትን የበለጠ ለማሳካት የሚከተሉትን የመግባቢያ ክህሎቶች ማዳበር ያስፈልጋል እነሱም

ሀ. መቻቻል፡- የማንወደውን ዘይቤ /ዕምነት/ ልምድ መቀበል

ለ. ማካፈል፡- ያለንን ዕውቀት ማካፈል /ያለንን ነገር ለሌላው እንዲጠቀምበትፈቃደኛ መሆን/

ሐ. አዛኝ መሆን፡- ሌሎች ሰዎች ችግር ሲያጋጥማቸው ችግሩን እንደራስ ማየትና በመገንዘብ የሚቃለልበትን መንገድ መፈለግን ያካትታል፡፡

መ. መደራደር፡- ሃሳብን ከሰዎች ጋር በነጻ ለመነጋገር መሞከር ናቸው፡፡

ተሽከርካሪ ከአምስት መሰረታዊ ነገር የተዋቀረ ነው እነሱም

1. ሞተር /ኢንጅን/
2. የኤሌክትሪክ ክፍሎች
3. ኃይል አስተላላፊ /ፓወር ትሬን/ ክፍሎች
4. ቻንሲ /የተሽከርካሪ መቆጣጠርያ ምቾት ጠባዊ ክፍሎች/
5. የተሽከርካሪ አካል /ቦዲ/ ናቸው

**1. ሞተር፡-** ማለት በተለያየ ዘዴ የአየርና የነዳጅ ድብልቅ ወይም አየር ብቻ በማስገባት በማመቅና በማቀጣጠል የተፈጠረውን ሙቀት ወደ ሜካኒካል ኃይል በመለወጥ ተሽከርካሪ ከቦታ ወደ ማንቀሳቀስ የሚያስችል ኃይል የሚፈጥር መሳሪያ ነው፡፡

ለሞተር መደረግ ያለበት ጥንቃቄ

- ሞተሩን ከማስነሳት በፊት በቂ ንፁህና ተገቢ ውፍረቱን የሞተር ዘይት መኖሩን ዘወትር ማየት
- በራዲያተር ውስጥ በቂ ውሃ መኖሩን ማረጋገጥ
- ሞተር ስናስነሳ ነዳጅ ሰጠት አለማድረግ በሚኒሞ /በአይድል/ ከ 3-5 ደቂቃ ማራት
- ተሽከርካሪ በጎ ላይ እያለ የሙቀትና የዘይት ጌጅ መከታተል
- ለረጅም ጊዜ ሲሰራ የዋለን ሞተር ከማጥፋት በፊት ከ3-5 ደቂቃ በአይድል ማሰራትና ማጥፋት
- ሞተሩን በማንዋሉ መሰረት ሰርቪስ ማድረግ

የሞተር ኃይል አጋዥ ክፍሎች

የሞተር ኃይል አጋዥ ክፍሎች የምንላቸው ሞተር ኃይል እንዲፈጥር የሚያግዙት ሲሆኑ እነሱም

1.1. የነዳጅ አስተላላፊ ክፍሎች
1.2. የማቀዝቀዣ ክፍሎች
1.3. የዕሳት አቀጣጣይ ክፍል ናቸው

### *1.1. የነዳጅ አስተላላፊ ክፍሎች*

ሞተር በነዳጅ አጠቃቀም በሁለት ይከፈላል እነሱም

1. የቤንዚን ሞተር
2. የናፍጣ ሞተር ናቸው

የቤንዚን ሞተር ነዳጅ አስተላላፊ ክፍሎችና ተግባራቸው

የነዳጅ ታንከር /ሰልባትዬ/፡- ሞተር የሚጠቀመውን ነዳጅ አጠራቅሞ የሚይዝልን ክፍል ነው፡፡

የነዳጅ መስመር፡- ታንከር ውስጥ ያለው ነዳጅ ወደ ካርቡሬተር የሚሄድበት ክፍል ነው፡፡

የነዳጅ ማጣሪያ /ፊልትሮ/፡- ቤንዚን ውስጥ ያለውን ነዳጅ የሚያጣራልን ክፍል ነው፡፡

የነዳጅ ፖንፕ፡- ታንከር ውስጥ ያለውን ነዳጅ የሚስብልንና ወደ ካርቡሬተር የሚያደርስልን ነው፡፡

## የካርቡሬተር ዋና ዋና ክፍሎችና ተግባራቸው

**ቾክ ቫልቭ፡-** በካርቡሬተር በላይኛው ክፍል የሚገኝ ሲሆን ወደ ሲሊንደር እርጥበት አዘል አየር እንዳይገባ እና ነዳጅ እንዲበዛ በማድረግ ሞተር ቶ እንዲነሳ የሚያደርግ ክፍል ነው፡፡

**ቬንቹሪ፡-** በካርቡሬተር ውስጥ የሚገኝ ጠባብ ክፍል ሲሆን አየርና ቤንዚን የሚቀላቀልበት ክፍል ነው፡፡

**ትሮትል ቫልቭ፡-** ከነዳጅ መስጫ ፔዳል ጋር የተያያዘ ሲሆን አንደኛ ነዳጅ አሰጣጥ ወደ ሲሊንደር አየርና ቤንዚን የሚያስገባ ነው፡፡

የናፍጣ ሞተር ነዳጅ አስተላላፊ ክፍሎች

1. የነዳጅ ታንከር /ሳልባትዬ/
2. የነዳጅ መስመር
3. የነዳጅ ማጣሪያ
4. ፊድ /መጋቢ/ ፓንፕ
5. ኢንጄክሽን /ፓንፕ እኛቶሪ/
6. ኃይፐሬዠር ላይን /ካኔታ/
7. ኢንጆክተር ኖዝል /እኛቶሪ/

8. መላሽ መስመር
9. ካንዲሊቲ /ግሎውፕለዝ/

## 1.2. የማቀዝቀዣ ክፍል

ሞተር በሁለት አይነት መንገድ ይቀዘቅዛል

1. በውኃ የሚቀዘቅዝ /ወተር ኩልድ/ ሞተር
2. አየር የሚቀዘቅዝ /ኤርኩልድ/ ሞተር ናቸው፡፡

በውሃ የሚቀዘቅዝ የማቀዝቀዣ ክፍሎችና ተግባራቸው

ራዲያተር፡- ሞተር የሚቀዘቅዝበትን ውኃ የሚይዝልንና ከሞተር ሞቆ የተመለሰው ውኃ የሚቀዘቅዝበት ክፍል ነው፡፡

የራዲያተር ክዳን፡- ራዲያተር ውስጥ ያለው ውኃ እንዳይፈስና በአነስተኛ ሙቀት ውኃ እንዳይፈላ ያደርጋል፡፡

የውኃ ፓንፕ፡- ራዲያተር ውስጥ ውኃ በመሳብ ወደ ወተር ጃኬት የሚያደርስልን ክፍል ነው፡፡

ቲርሞስታት፡- ሞተር የተወነ የሙቀት ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ውሃ ከራዲያተር ወደ ሞተር እንዳይዘዋወር ዘግቶ የሚይዝ ክፍል ነው፡፡ እንዲሁም ሞተር የተወሰነ የሙቀት ደረጃ ላይ ሲደርስ በመክፈት ውሃ ወደ ሞተር እንዲገባ ያደርጋል፡፡

ወሳጅ መስመር /የታችኛው ማኒኮቴ/፡- ቀዝቃዛው ከራዲያተር ወደ ሞተር /ወተር ጃኬት/ የሚሄድበት ክፍል ነው፡፡

ወተር ጃኬት፡- በሞተር ውስጥ ውሃ የሚዘዋወርበትን ክፍል ነው፡፡

መላሽ መስመር /የላይኛው ማኒኮቴ/፡- ከሞተር የሞቀው ውሃ ወደ ራዲያተር የሚመለስበት ክፍል ነው፡፡

ቬንትሌተር /ፋን/፡- ከራዲያተር ሞቅ የተመለሰውን ውሃ የሚያቀዘቅዝልን ክፍል ነው፡፡

ሽራውድ፡- የሞቀውን ውሃ ቬንትሌተር እየቀዘፈ በሚያቀዘቅዝበት ጊዜ የሚቀዝፈው አየር ራዲያተር ላይ ብቻ እንዲያርፍ የሚያደርግ ክፍል ነው፡፡

### *1.3. የማለስለሻ ክፍል*

ዘይት በሁለት አይነት መንገድ ወደ ሞተር ይደርሳል እነሱም

1. በክራንክ ሻፍት ስርጭትና
2. በዘይት ፓንፕ ግፊት ናቸው።

ዘይት ወደ ሞተር ሊሰራጭ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል እነሱም

1. ሰበቃን ይቀንሳል
2. ሙቀትን ይቀንሳል
3. ድምጽን ይቀንሳል
4. ቆሻሻን ያጸዳል
5. ዝገትን ይከላከላል
6. በሞተር ውስጥ ጥሩ ዕመቃ እንዲኖር ያደርጋል።

በማለስለሻ ክፍሎች ተግባራቸው

1. ሶቶኮፓ /ኦይል ፓን/፡- ሞተር የሚለሰልስበትን ዘይት የሚይዝልን ክፍል ነው።
2. የዘይት ፓንፕ፡- ዘይት ከሶቶኮፓ በመሳብ ወደ ኦይል ጋለሪ የሚደርስልን ክፍል ነው።
3. ኦይለ ስክሪን፡- በሶቶ ኮፓ ውስጥ የሚገኙ ትላልቅ ቆሻሻዎች እያጣራ የሚያስወግድ ክፍል ነው።
4. የዘይት ማጣሪያ፡- ከኦይል እስክሪን አልፎ የሚመጣን አነስተኛ ቆሻሻ የሚያጣራ ክፍል ነው።
5. ሊቤሌ /ዲፕስቲክ/፡- በሶቶኮፓ ውስጥ ያለውን ዘይት መጠኑን፣ መቆሸሽና አለመቆሸሹን መወፈርና መቅጠኑን የሚነግረን
6. ኦይል ጋለሪ፡- በሞተር ውስጥ ዘይት የሚዘዋወርበት ክፍል ነው
7. የሞተር ዘይት አመልካች ጌጅ፡- ሞተር ከተነሳ በኃላ ወደ ሞተር ክፍሎች ውስጥ በቂ ዘይት ስርጭት መኖሩንና ያለመኖሩን የሚነግረን ክፍል ነው።

## 2. በተሽከርካሪ ላይ የሚገኙ የኤሌክትሪክ ዘዴዎች

1. ሞተርን የማስነሳት ዘዴ /ስታርቲንግ ሲስተም/
2. ባትሪን የመሙላት ዘዴ /ቻርጂንግ ሲስተም/
3. መቆጣጠርያ ዘዴ /ኢግኒሽን ሲስተም/

***ሞተር የማስነሳት ዘዴ***

1. ባትሪ፡- በውስጡ 35ኀ አሲዱ 65ኀ ውሃ በመያዝ የኬሚካል ኃይልን ወደ ኤሌክትሪካል ኃይል በመለወጥ ኃይል የሚያመነጭልን ክፍል፡፡
2. የሞተር ማስነሻ ቁልፍ፡- ባትሪ ላይ ያለውን ኃይል ወደ ኤሌክትሪክ ክፍሎች የሚያስተላልፍና የሚያቋርጥ ክፍል ነው፡፡
3. ስታርተር ሞተር /ሞተሪኖ/፡- ከባትሪ የተቀበለውን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላይ ዊልን /ቮላኖን/ በማዞር ወደ ሜካኒካል ኃይል የሚለውጥልን /ሞተር እንዲነሳ የሚያደርግልን ክፍል ነው፡፡

***ባትሪን የመሙላት ዘዴ***

1. ባትሪ
2. የሞተር ቁልፍ
3. ጀነሬተር /ዲናሞ/፡- በችንጋ አማካኝነት ከኮሎ እየተነዳ የማያገኘውን የመካኒካል ኃይል ወደ ኤሌትሪካል ኃይል የሚለውጥልን ክፍል ነነው፡፡ በዋናነት ባትሪን ቻርጅ ያደርግልናል፡፡
4. ሬጉሌተር፡- ከነጀሬተር የተቀበለውን ኤሌትሪክ ለተለያዩ የኤሌትሪክ ክፍሎች ያከፋፍላል፡፡
5. ፊውዝ፡- ከተለያዩ የኤሌክትሪክ ክፍሎች ፊት በመገጠም ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል በሚወጣበት ወቅት ራሱን በማቃጠል ኤሌክትሪክ እንዲቋረጥ የሚያደርግልን ክፍል ነው፡፡

የእሳት አቀጣጣይ ክፍሎች

1. ባትሪ
2. የሞተር ማሽነሻ ቁልፍ
3. ቦቢና /ኢግኒሽን ኮይል/፡- ከባትሪ ተቀበለውን አነስተኛ ኃይል ወደ ከፍተኛ ኃይል የሚለወጥ ክፍል ነው፡፡

4. አባንስ /ዲስትሪቢውተር/፡- ከቦቢና የተቀበለውን ከፍተኛ ኃይል ጊዜውንና ሰዓቱን በመጠበቅ ለካንዴላ የሚያስተላልፍ ክፍል ነው፡፡
   ገፅ 11
5. ካንዴላ /ስፓርክ ፕለግ/፡- ከአባንስ የተቀበለውን ኃይል ሲሊንደር ላይ የታመቀው አየርና ነዳጅ ላይ እሳት ይረጫሉ፡፡

## 3. ኃይል አስተላላፊ ክፍሎች

ኃይል አስተላላፊ ተግባራቸው ሞተር ላይ የተፈጠረው ኃይል በመቀባበል ጎማ ድረስ ማድረስ ሲሆን እያንዳንዳቸው ሚተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

1. ፍሬሲዮን፡- ከሞተር የተቀበለውን ኃይል ወደ ካንቢዮ /ጊርቦክስ/ ማስተላለፍ ማቋረጥ ነው፡፡
2. ካንቢዮ /ጊርቦክስ፡- ከካንቢዮ የተቀበለውን ኃይል ወደ ትራንስሚሲዮን የሚያስተላልፍ ሲሆን የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል እነሱም፡-
    1. ጉልበት /ከባድ ማርሽ/ 1ኛ 2ኛ እና የኋላ ማርሽ
    2. ፍጥነት /ቀላል ማርሽ/ 3ኛ 4ኛ………….. ወዘተ
    3. የአቅጣጫ ለውጥ /የኋላ ማርሽ/ ናቸው፡፡

3. ትራንስሚሲዮን /ፕሮፐራል ሻፍት/፡- ከካንቡ የተቀበለውን ኃይል ለዱፈረንሻ የሚያስተላልፍ ሲሆን ሁለት አይነት ጃይንቶች አሉት እነሱም ዩኒቨርሳል ጃይንቶች ስሊፕጆይንት ናቸው፡፡

4. ዲፈረንሻል፡- ከትራንስሚሲዮን የተቀበለውን ኃይል ወደ አክሰል /ሸሚያስ/ የሚያስተላልፍ ሲሆን የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡ እነሱም

- ከትራንስሚሲዮን የተቀበለውን ቀጥተኛ ዙር ወደ አክሰል /ጎማ/ ዙር ይለውጣል፡ ፡
- ተሽከርካሪው ቀጥ ባለ መንገድ ላይ ሲጓዝ ለሁሉም ጎማዎች እኩል ኃይልን ያስተላልፋል፡፡
- ተሽከርካሪው በሚታጠፉበት ጊዜ ጎማ ጠባብ ዙር ለውስጠኛው ጎማ ሰፊ ዙር እንዲዞር በማድረግ የመኪናው ጎማ ይጠብቃል፡፡

5. ሺሚያስ /አክሰል/፡- ከዲፈረንሻል የተቀበለውን ኃይል ለጎማ በማድረስ ተሽከርካሪው እንዲጓዝ ያደርጋል፡፡

## የተሽከርካሪ ተሸካሚ ክፍሎች

1. ባሌስትራ /ሊፍስፐሪንግ/
2. ጥቅል ሞላ /ኮይል እስፐሪንግ/
3. አሞርዛተር /ሾክ አብዞርቨር/
4. ቶርሽን ባር

## የተሽከርካሪ መቆጣጠርያ ክፍሎች

1. መሪ፡- ተሽከርካሪያችንን ወደፈለግንበት አቅጣጫ የምንቆጣጠርበት ክፍል ነው፡፡
2. የሞተር ማስነሻ ቁልፍ፡- የተሽከርካሪያችንን የኤሌክትሪክ ክፍሎችና ሞተርን ምናስነሳበት የምናጠፋበት ክፍል ነው፡፡
3. ፍሬሲዮን፡- ፍጥነት የሚጨምርበት ባላንስ ምንሰራበት ሞተር እንዳታጠፋ የማናደርግበት ክፍል ነው፡፡
4. የነዳጅ መስጫ ፔዳል፡- የተሽርካሪን ፍጥነት የምንጨምርበትና የምንቀንስበት የመቆጣጠርያ ክፍል ነው፡፡
5. ፍሬን፡- ተሽከርካሪያችንን ፍጥነት የምንቀንስበትና ተሽከርካሪያችንን ሙሉ በሙሉ የምናቆምበት ክፍል ነው፡፡

## የመገናኛ መሳሪያዎች

1. ክላክስ /ጡሩንባ/
2. የግንባር መብራት
3. የፍሬን መብራት
4. የኃላ ማርሽ መብራት
5. የስሌዳ መብራት
6. ማስጠንቀቂያ /ሃዛርድ/ መብራት
7. የጎን መብራት
8. ማቆሚያ /ፓርኪንግ/ መብራት
9. ፍሬንቻዎች

### የፍሬቻዎች ጥቅም

#### የቀኝ ፍሬቻ

1. ከግራ ረድፍ ወደ ቀኝ ለመለወጥ
2. ወደ ቀኝ ለመታጠፍ
3. ለመቆም
4. ከኋላ ያለን ተሽከርካሪ ለማስቀደም
5. ወደ ቀኝ ዞሮ ለመመለስ

#### የግራ ፍሬቻ

1. ከቀኝ ወደ ግራ ረድፍ ለመለወጥ
2. ወደ ግራ ለመታጠፍ
3. ወደ ግራ ዞሮ ለመመለስ
4. ከቆምንበት ለመነሳት
5. ከፊት ያለን ተሽከርካሪ አስቀድመኝ የሚል መልእክት ለማስተላለፍ

## የትዕይንት መቆጣጠርያ መሳሪያዎች

1. የግናባር መብራት
2. የፀሀይ ጨረር መከላከያ
3. የዝናብ መጥረጊያ
4. የጋቢና ውስጥ መብራት
5. የጎንና የመሃል ስፖኪዮ
6. የጉም የጭጋግ ማቅለጫ ናቸው።

# አለማቀፍ የመንገድ ዳር ምልክቶች

አለማቀፍ የመንገድ ዳር ምልክቶች በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ እነሱም

1. የሚያስጠነቅቁ     2. የሚቆጣጠሩ     3. መረጃ ሰጪ ሲሆኑ

1. **የሚያስጠነቅቁ፡-** ቅርጻቸው ሶስት መዓዛን መደባቸው ነጭ ዙሪያቸው በቀይ ቀለም የተከፈፈ ሲሆን የሚያስተላልፉት መልዕክት የተጻፈው በጥቁር ቀለም ሆኖ በቀለበት፣ በጽሁፍ በስዕል ሊሆን ይችላል፡፡

| የሚያስጠነቂቁ ምልክቶች | | |
|---|---|---|
| 1 | ጠባቢ ድልዲይ |  |
| 2 | መንገድ የምጠግኑ |  |
| 3 | መገናኛ መንገድ |  |
| 4 | ወደ ፊትነ ወደ ግራ የሚተጠፍ መንገድ |  |
| 5 | ወደ ፊትና ወደ ቀኝ የምጠተፍ መንገድ |  |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | ወደ ፍትና ወደ ቀኝ ብቻ የምሄድ መንገድ |  |
| 7 | የተበለሻ መንገድ |  |
| 8 | ወደ ግራ የምተጠፈ መንገድ የቀኝ ረድፍ ይዘህ ተጠንቅቀህ እለፍ |  |
| 9 | ወደ ቀኝ የምጠፍ መንገድ የቀኝ ረድፍ ይዘህ ተጠንቅቀህ እለፍ |  |
| 10 | መጀመሪያ ወደግራ ቀጥሎ ወደ ቀኝ የምተጠፍ |  |
| 11 | መጀመሪያ ወደ ቀኝ ቀጥሎ ወደ ግራ |  |
| 12 | በሁለቱም በኩል እያጠበባ |  |
| 13 | መዝግያ ያለዉ የባቡር ሀዲድ |  |
| 14 | መዝግያ የሌለው የባቡር ሀዲድ |  |
| 15 | አደገኛ ቁልቁለት |   |

| | | |
|---|---|---|
| 16 | በተለያያ ርቀት የባቡር ሐዲድ<br>• 3 ሰረዝ 250 ሜ<br>• 2 ሰረዝ 170 ሜ<br>• 1 ሰረዝ 100 ሜ |  |
| 17 | ባለ አንድ መቋረጫ |  |
| 18 | ባለ ሁለት መቋረጫ |  |
| 19 | እግራኛ ማቋረጫ |  |
| 20 | ት/ቤት |  |
| 21 | አንድ አቅጣጫ የነበራ ለግዜው ሁለት አቅጣጫ |  |
| 22 | የሚያንሸራትት መንገድ |  |
| 23 | አደገኛ መንገድ |  |
| 24 | የትራፊክ ማብራት ከፊት ስለአለ ተጠንቀቅ |  |

| | | |
|---|---|---|
| 25 | ሀይለኛ ንፋስ |  |
| 26 | አደገኛ ኩርባ በቀስቱ አቅጣጫ |  |
| 27 | አደባባይ ከፊት |  |
| 28 | ሁለት አንገድ ወደ አንድ ይቀየራል |  |
| 29 | የሚፈናጠር ጠጠር |  |
| 30 | የትራፊክ ፊልሰት ስለምበዛ ርቀት ተብቀህ |  |
| 31 | የጋማ ከብት ስለሚተላለፉ |  |
| 32 | አካል ጉዳተኞች ስለምተላለፉ |  |
| 33 | የእርሻ ማሽኖች ስለምተላለፉ |  |

| | | |
|---|---|---|
| 34 | ዝግዛግ መንገድ |  |
| 35 | የእሳት አደጋ መኪና ስምያገጥምህ |  |
| 36 | የጭነት ተሽከርካሪ ስለምያገጥመህ |  |
| 37 | ልጆች መጨወቻ |  |
| 38 | መንገዱ ሁለት ቦታ ስለምከፈል |  |
| 39 | ሁለት ቡታ ተከፍሎ የነበራ ወደ አንድ |  |
| 40 | ከፊት ቁም ምልክት ስለምያገጥመህ |  |
| 41 | ከፊት ቅድምጣ ስጥ የምል ምልክት ስለምያገጥመህ |  |
| 42 | ወደ ቀኝ መንታ መንገድ |  |
| 43 | ከፊት ወደ ቀኝኛ ወደ ግራ |  |

| | | |
|---|---|---|
| 44 | ከፊት በጨርቅ የትራፊክ ምልክት የሚያስተላልፊ |  |
| 45 | በቀኝ በኩል የባቡር ሐዲድ መቋረጫ |  |
| 46 | የአስፋልት መንገድ መጨረሻ |  |
| 47 | የሚነድ መንገድ |  |
| 48 | የሚቀሳቀስ ድልዲይ |  |
| 49 | ገደል አፋፍ ስለምያገጥምህ |  |
| 50 | የመንገዱ ጠዝር የሚነድ ስለሆና |  |

2. **የሚቆጣጠሩ፡-** የመንገድ ዳር ምልክቶች ከሚያስተላልፉት መልዕክት የተነሳ በሶስት ንዑሳን ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡ እነሱም

2.1. የሚከለክሉ /የሚወሰኑ/

- ክብ ቅርፅ ፧ ዙርያ ቀይ ቀለም ሆኖ መልዕክት በጥቁር ቀለም ያስተላልፋሉ

| የሚከለክሉ ምልክቶች | | |
|---|---|---|
| 1. | ማንኛዉም ተሽከርካሪ ማለፍ የተከለከላ |  |

| | |
|---|---|
| 2. በዚህ አቅጣጫ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 3. ወደ ቀኝ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 4. ወደ ግራ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 5. ቀድሞ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 6. ሁለት እግር በላይ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 7. ሞተር ሳይክል ማለፍ የተከለካለ |  |
| 8. በሞተር ሀይል የምቀሳቀስ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 9. ጠቅላላ ክብደቱ ከ705 ቶን በላይ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 10. ከ20 ቶን በላይ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 11. በግራ በኩል ዞሮ መመለስ የተከለከላ |  |
| 12. ሳይክል ማለፍ የተከለከላ |  |
| 13. በእንስሳ የሚጎተት ማለፍ የተከለከላ . |  |

| | |
|---|---|
| 14. በሰው እጅ የሚገፋ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 15. እግረኛ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 16. የአክስል ክብደት ከ8000 ኪ.ግ ባላይ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 17. ጠቅላላ ስፋቱ ከ20 ሜ በላይ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 18. ጠቅላላ ከፍታ ከ40ሜትር በላይ ማለፍ የተከለከላ |  |
| 19. የከተማ ክልልነ መግቢያ |  |
| 20. የከተማ ክልል መጨረሻ |  |
| 21. ጡሩምባ ማሰማት የተከለከላ |  |
| 22. ማቆም የተከለከላ |  |
| 23. ለረጅም ግዜ ማቆሚ የተከለከላ |  |
| 24. ከፊት ለሚመጣ ቅዲምያ ስጥ |  |
| 25. ጉምሩክ |  |

| | |
|---|---|
| 26. ማቅም የምክለክል ምልክት መጨረሻ |  |
| 27. ከተገለጸው ርቀት በታች ተጠግቶ ማሽከርከር የተከለከለ |  |
| 28. ማቆም የተከለከለ |  |
| 30. ተቀጣጣይ ጭነት ይዞ የሚያልፉ ስለሆና ማለፍ የተከለከለ |  |
| 32. የጭነት ተሽከርካሪ ማለፍ የተከለከለ |  |
| 33. የተበለሸ ጎትቶ ማለፍ የተከለከለ ነው |  |
| 37. ጠቅላለ ርዝመቱ ከ10 ሜ በላይ የሆና ማለፍ የተከለከለ |  |

## 2.2. የሚያስገድዱ

- ቅርጻቸው ክብ ወይም አራት ማዕዘን ፤ ቀለማቸው ውሃ ሰማያዊ ፤ የሚያስተላልፉት መልዕክት በነጭ ቀለም

| | የሚያስገድዱ ምልክቶች | |
|---|---|---|
| 1. | ወደ ግራ እለፍ |  |
| 2. | ወዳ ፊት እለፍ |  |
| 3. | ወደ ቀኝ እለፍ |  |
| 4. | ወደ ግራ ወይም ወዳ ፊት እለፍ |  |
| 5. | ወዳ ቀን ወይም ወዳ ፊት እለፍ |  |
| 6. | ወዳ ቀኝ ወይም ወዳ ግራ ብቻ እለፍ |  |
| 7. | ወዳ ግራ እለፍ |  |

| | | |
|---|---|---|
| 8. | ወዳ ቀኝ እልፍ |  |
| 9. | ቀስቱ በሚያሰይ አቅጣጫ እለፍ |  |
| 10. | |  |
| 11. | |  |
| 12. | ቀስቱ በሚያሰይ አደባበይ ዙር |  |
| 13. | ሳይክል ብቻ እለፍ |  |
| 14. | |  |
| 15. | አነስተኛ የፍጥነት መጠን |   |

| | | |
|---|---|---|
| 16. | አነስተኛ የፍጥነት መጠን መነሻ |  |
| 17. | ለእግራኛ የተፈቀደ |  |
| 18. | ለማቆም የተፈቀዳ አቅጣጫ |  |

2.3. ቅድሚያ የሚያሰጡ ናቸው

2.1. የሚከለከሉ/የሚወስኑ/፡- ቅርጻቸው ክብ ዙሪያቸው የተከበበው በቀይ ቀለም ሲሆን መደባቸው መልዕክት የተጻፈው በጥቁር ቀለም ሆኖ በጽሁፍ በቀስት በስዕል ሊሆን ይችላል፡፡

2.2. የሚያስገድዱ፡- ቅርጻቸው ክብ መደባቸው ሰማያዊ የሚያስተላልፉት መልዕክት የተጻፈው በነጭ ቀለም ሆኖ በስዕል በጽሁፍ በቀስት ሊሆን ይችላል፡፡

2.3. ቅድሚያ የሚያሠጡ፡- ቅርጻቸው የተለያየ ሲሆን የሚያስተላልፉት መልዕክት ቅድሚያ ስጥ የሚል ነው፡፡

| | ቅድሚያ የሚያሠጡ | |
|---|---|---|
| 1. | ቆማ ቅድሚያ ሰጥተህ እለፍ |  |
| 2. | ቅዲምያ አለህ እለፍ |  |

| | | |
|---|---|---|
| 3. | ቅዲምያ አለህ የሚል መጨረሻ |  |
| 4. | ከፊት ለምመጣ ቅዲምያ ስጥ |  |
| 5. | በመገናኛ መንገድ ቅድሚያ ስጥ |  |

3. መረጃ ሰጪ፡- የመንገድ ዳር ምልክቶች ቅርጻቸው አራት መዓዘን ሲሆን ከሚያስተላልፉ መልዕክት የተነሳ በሁለት ይከፈላሉ እነሱም፡-

## 3.1. አገልግሎት ሰጪ አመልካች

- አገልግሎት ማግኘት የምንችልባቸውን ቦታዎች የሚጠቁሙን ናቸው

| መረጃ ሰጪ | | |
|---|---|---|
| 1. | ነዳጅ ማደያ |  |
| 2. | የጉዞ መነሻ ቦታ |  |
| 3. | ሆቴል |  |
| 4. | እረፍት መውሰጃ ቦታ |  |
| 5. | ሪስቶራንት |  |

| | | |
|---|---|---|
| 6. | ካፍቴሪያ |  |
| 7. | ስልክ |  |
| 8. | ገራጅ |  |

## 3.2. አቅጣጫ አመልካች

- መንገዶች ወዴት አቅጣጫ እንደሚወስዱን የሚነግሩንና መንገዱ ዘላቂ መሆኑንና አለመሆኑን ይነግሩናል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የመንገድ አቅጣጫና ርቀት | <br><br> |

# አለም አቀፍ የመንገድ ላይ መስመሮች /ቅቦች/ አገልግሎት

1. አንድ አሽከርካሪ የት ቦታ ላይ መታጠፍ እንዳለበትና እንደሌለበት ይገልጻል፡፡
2. ባለ አንድ አቅጣጫን መንገድ እኩል ለሁለት ይከፍላል
3. የእግረኛ መሻገሪያ ዜብራን ያሳውቃል
4. የአንድን መንገድ ስፋት ዳርና ዳሩን እንዲሁም መሀሉን ያሳውቃል
5. የትራፊክ መብራት አካባቢ መቆም ያለብንን ቦታ ያሳውቀናል
6. ባለአንድ አቅጣጫን መንገድ በረድፍ ይከፋፍላል
7. የመንገድ ዳር ምልክት መትከል በማይቻልበት ቦታ የመንገድ ዳር ምልክትን ተክቶ ይሰራል

አለምአቀፍ የመንገድ ዳር መስመሮች በሁለት ይከፈላሉ

እነሱም፡-

1. በመንገዱ አቅጣጫ
2. በመንገዱ አግድመት የሚሰመሩ ናቸው

በመንገድ አቅጣጫ የሚሰመሩ መስመሮች የምንላቸው

ሀ. በመንገዱ አቅጣጫ ድፍን /ያልተቆራረጠ/ መስመር ሲሰመርና

ለ. በመንገዱ አቅጣጫ የተቆራረጠ መስመር ሲሰመር ነው



በመንገዱ አቅጣጫ የተቆራረጠ መስመር ሲሰመር የሚያስተላልፈው መልዕክት

1. መንገዱ ለማሽከርከር አመቺ መሆኑ
2. መንገዱን የትራፊክ መጨናነቅ የሌለው መሆኑ ሲሆን

ስለዚህ በመንገዱ አቅጣጫ የተቆራረጠ መስመር ሲሰመር መስመሩን አቋርጦ መታጠፍ ዞሮ መመለስ እና ከፊት ያለን ተሽከርካሪ መቅደም አይቻልም






## በመንገዱ አግድመት የሚሰመር መስመር

- ለእግረኞችመሻገሪያ የሚያገለግል ዜብራ
- እግረኞች በሚሻገሩበት ጊዜ ክላክስ መንፋት የተከለከለ ነው
- በእግረኛ መሻገሪያ ዜብራ በ12 ሜ ክልል ውስጥ ተሽከርካሪው አቁሞ መሄድ አይቻልም



# አለም አቀፍ የትራፊክ ማስተላለፊያ መብራቶች

በሚሰጡት አገልግሎት በሁለት ይከፈላሉ እነሱም

1. የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራትና
2. የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት ናቸው

## እግረኛ ማስተላለፊያ መብራት

ቀይ፡- የሰው ምስል ያለበት የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራት ሲበራ እግረኞች ይቆማሉ ተሽከርካሪዎች ያልፋሉ



አረንጓዴ፡- የሰው ምስል ያለበት የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራት ሲበራ እግረኞች ያልፋሉ ተሽርካሪዎች ይቆማሉ፡፡



## የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት

የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት በሶስት ይከፈላሉ እነሱም ከላይ ወደ ታች ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ ሲሆኑ በአበራር ቅደም ተከተላቸው በአራት ይከፈላሉ ቅደም ተከተል

ቀይ → ቀይና ቢጫ → አረንጓዴ → ቢጫ ነው

1. ቀይ፡- የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት ሲበራ የደረሰ ተሽከርካሪ አስድሞ የሚሄድበትን አቅጣጫ በመምረጥ መቆም አለበት



2. ቀይ እና ቢጫ፡- በአንድነት ሲበሩ በቀይ መብራት ቆመው የነበሩ ለመሄድ ሲዘጋጁ ከኋላ የሚመጡት ደግሞ ይቆማሉ፡፡



3. አረንጓዴ፡- መብራት ሲበራ አስቀድመው በመረጡት አቅጣጫ መሔድ አለባቸው



4. ቢጫ፡- መብራት ሲበራ አደባባይ ውስጥ የገቡት በፍጥነት ለቀው ሲወጡ የእግረኛ ዜብራውን ያላለፉት ግን ይቆማሉ፡፡



1. ቀይ ብቻውን፡- ብልጭ ጥፍት /ቦግ እልም/ እያለ ሲበራ የደረሰ ተሽከርካሪ በመቆም መገናኛ መንገድ ላይ ላሉ ቅድሚያ በመስጠት ማለፍ አለበት፡፡
2. ቢጫ ብቻውን፡- ብልጭ ጥፍት /ቦግ እልም/ እያለ ሲበራ የደረሰ አሽርካሪ ፍጥነቱን በመቀነስ መስቀለኛ መንገድ ውስጥ ላሉ ቅድሚያ በመስጠት ማለፍ አለበት፡፡

## ቅድሚያ መስጠት ያለበት

- ከመጋቢት መንገድ ወደ ዋና መንገድ ስንገባ ቅድሚያ መስጠት አለበት
- ከቆምንበት ስንነሳ በመንገዱ ውስጥ ላሉ ተሽርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለብን
- ከግቢያችን ወደ ዋና መንገድ ስንወጣ ቅድሚያ መስጠት አለብን
- ቁልቁለት ስንወርድ ዳገት ለሚወጣ ተሽርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለብን ነገር ግን የህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተሽከርካሪ ከሆነ ዳገት ሲወጣ ቁልቁለት ሲወርድም ቅድሚያ አለው
- መስቀለኛ መንገድ ላይ እኩል ብንደርስ በቀኝ በኩል ያለው ተሽከርካሪ ቅድሚያ አለው

## ዳሽ ቦርድ ላይ ያሉ መሳሪያዎች /ጌጆች/

1. ኦዶ ሜትር፡- ተሽርካሪ ተመርቶ ጉዞ ከጀመረበት ጊዜ እስካሁን ምን ያህል ኪ.ሜ እንደተጓዘ የሚመለከት መሳሪያ ነው
2. ትሪፕ ኦዶ ሜትር፡- ተሽከርካሪው እንደ ጉዙ ሲጓዝ ምን ያህል ከ.ሜ እንደተጓዘ የሚመዘግብ መሳሪያ ነው
3. ታኮ ሜትር /ሞተር ፍጥነት አመልካቾች/፡- የሞተርን ዙር በደቂቃ ምን ያህል እንደሚዞር





4. ስፒዶ ሜትር /ተሽርካሪ ፍጥነት አመልካች/፡- ተሽርካሪው በሰዓት ምን ያህል ኪ.ሜ እየተጓጓ እንዳለ ለአሽከርካሪው ሚያመለክት መሳሪያ ነው።
5. የሙቀት መጠን አመልካች፡- ሞተሩ ሲሰራ የሚችልበት ጤናማ የሙቀት ክልል ውስጥ መሆኑንና ያለመሆኑን ለአሽከርካሪዎች የሚያመለክት መሳሪያ ነው






6. የነዳጅ መጠን አመልካች፡- በነዳጅ መያዣ ጋን ውስጥ በቂ የነዳጅ መጠን መኖሩንና ያለመኖሩን ለአሽከርካሪዎች የሚያሳውቀው ለሌሎችም የሚገኙ ይሆናል

## የደህንነትና የምቾት መፍጠርያ መሳሪያዎች

1. አሽከርካሪ ወንበር
2. የወንበር የጭንቅላት መደገፊያ
3. የደህንነት ቀበቶ
4. የአየር ከረጢት /ኤርባግ/
5. የአየር ማቀዛዘዣና ማሞቂያ

## የፍጥነት ገደብና የርቀት ወሰን በአገራችን

ማንኛውም አሽከርካሪ ከፊት ለፊቱ ካለው ተሽከርካሪ እንደፍጥነቱ ሁኔታ መራቅ ያለበት የርቀት ወሰን እንደሚከተለው ነው፡፡

| በፍጥነት በኪ/ሜ | መራቅ ያለበት ሜትር |
|---|---|
| 1. በሰዓት 40-50 | 20 ሜትር |
| 2. በሰዓት 50-60 | 25 ሜትር |
| 3. በሰዓት 70-80 | 30 ሜትር |
| 4. በሰዓት 9፤0-10 | 36 ሜትር |
| 5. በሰዓት 40-50 | 43 ሜትር |
| 6. በሰዓት 11፤00-12.00 | 48 ሜትር |
| 7. በሰዓት 13፣00-14፤00 | 55 ሜትር |
| 8. በሰዓት 150-160 | 58 ሜትር |

የአገራችን መንገድ የከተማ ክልልና ከከተማ ክልል ውጪ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ የፍጥነት ገደባቸው እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

| የተሽከርካሪ ጠቅላላ ክብደት | የመንገዱ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 1ኛ ደረጃ መንገድ | 2ኛ ደረጃ መንገድ | 3ኛ ደረጃ መንገድ | 4ኛ ደረጃ መንገድ |
| እስከ 3500 ኪ.ግ | 100 ኪ.ግ | 70 ኪ.ግ በሰዓት | 60 ኪ.ግ በሰዓት | 60 ኪ.ግ በሰዓት |
| ከ3500-7500 ኪ.ግ | 80 ኪ.ግ | 60 ኪ.ግ በሰዓት | 50 ኪ.ግ በሰዓት | 40 ኪ.ግ በሰዓት |
| ከ7500 ኪ.ግ በላይ | 70 ኪ.ግ | 50 ኪ.ግ በሰዓት | 40 ኪ.ግ በሰዓት | 30 ኪ.ግ በሰዓት |

## የአውቶቲክ ማርሽ አጠቃቀም

አውቶማቲክተሽከርካሪማርሽመምረጫ ዘንግ ላይ የሚገኙ ፊደሎችን አጠቃቀም በዝርዝር እንደሚከተለው ነው፡፡ እነርሱም

P- አሽከርካሪውን አቁሞ በሚሄድበት ወቅት የማርሽ ዘንጉን በፊደሉ ትክክል ማድረግ አለበት፡፡ የማርሽ እጀታው በዚህ ቦታ ላይ ሲሆን ጊርቦክስ እንዲቆልፍ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ተሽከርካሪው መንቀሳቀስ አይችልም ሞተሩንም በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ማንሳት ይቻላል፡፡

R- የተሽከርካሪውን አቅጣጫ ወደ ኋላ መቀየር ተፈለገበት ወቅት/የኋላ ማርሽ/ የማርሽ ዘንጉን በፊደሉ አቅጣጫ ትክክል ማድረግ ያስፈልጋል ነገር ግን ተሽከርካሪው ሙሉ ለሙሉ መቆሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

N- የማርሽ እጀታው በዚህ ቦታ ላይ ሲሆን ማርሹ ተላቋል ማለት ሲሆን ይህ ማለት በማንዋል ጊርቦክስ ላይ ዜሮ እንዳድረግ ማለት ነው፡፡

D- ተሽከርካሪው ወደ ፊት የሚሄድበት ጊዜ የማርሽ ዘንጉ በፊደሉ ትክክል መሆን አለበት፡

L- ተሽከርካሪው ወደ ፊት በሚሄድበት ጊዜ መጠቀም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ የማርሽ ዘንጉን በፊደሉ ትክክል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**በማሽከርከር ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ የተፈጥረጥ ሀጎች የሚባሉት**

1. መሬት ስበት
2. ኢነርሺያ
3. መምንተም
4. ሞመንተም
5. ሰበቃ
6. ሴንትሪፈውጋል ኃይል ናቸው፡፡

1. የመሬት ስበት ፡- ስበት ጎማን መሬት ቆንጥጦ እንዲይዝ የሚያደርግ ሃይል ነው ______ ዳገት ሲወጣ የመሬት ስበት የተሽከርካሪን ፍጥነት ይቀንሰዋል፡፡ ቁልቁለቱን ሲወርድ ደግሞ ፍጥነቱን ይጨምራል ስለዚህ ዳገት ሲወጣም ሆን

ቁልቁለት ሲወርድ ከባድ ማርሽ መጠቀምና ፍሬን በትንሹ መያዝ ተሽከርካሪን ለመቆጣጠር ይረዳል፡፡

2. የኢነርሺያ ህግ፡- ሌላ ተጨማሪ ሃይል እስካልመጣ ድረስ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ ነገሮች እንቅስቃሴያቸውን መቀጠል ይፈልጋሉ የቆሙ ነገሮች ደግሞ መቆየት ይፈልጋሉ፡፡ ይህ የኢነርሺያ ህግ ነው፡፡------------ ፍሬን ካልተያዘ፤ መሬቱ ወይም ሌላ ቋሚ ነገር ከፊት ካላገደ በስተቀር መጓዝ የጀመረ ተሽከርካሪ በኢነርሺያ ምክንያት ጉዞውን ይቀጥላል፡፡
   - ተሽከርካሪ ከጉዞ መንገድ ሲቆም ሰውና የተንጠለጠሉ ነገሮች ላይ አደጋ ሲደርስ ይችላል፡፡
3. ፖተንሺያል ሃይል፡- ነገሮች ባሉበት ቦታ ወይም ቅርፅ ምክንያት የሚኖራቸውን የተጠራቀመ ኃይል ፖተንሺያል ኢነርጂ ይባላል፡፡
4. የኬኔቲክ ኃይል፡- በእንቅስቃሴ ላይ ያለ ነገር የሚኖረው ኃይል ኬኔቲክ ኢነርጂ ይባላል፡፡ የተሽከርካሪ ፍጥነት በጨመረ ቁጥር ኬነቲክ ኢነርጂ ይጨምራል፡፡ የኬነቲክ ኢነርጂ በጨመረ ቁጥር የተሽከርካሪው ፍሬን የመያዝ ኃይል መጨመር አለበት፡፡
5. ሞመንተም፡- ሁለት ያልተመጣጠነ ኃይሎችን በአንድ ነገር ላይ በተቃራኒ አቅጣጫ ግፊታቸውን ሲያሳርፉ የሚንቀሳቀስ ነገር የያዘው ሃይል ሞመንተም ይባላል፡፡
6. ሰበቃ፡- አንድ ነገር ከሌላ ነገር ጋር ሲነካካ የሚፈጠረው ኃይል ሰበቃ ይባላል፡፡
   - ሰበቃ አንድ ነገር በሌላ ነገር ላይ እንዲቀሳቀስ ያደርጋል፡፡
   - ሰበቃ የሚከሰተው በመንገድና በጎማ መሀል፤ በፍሬን ውስጥ፤ በሞተር ውስጥ በኃይል አስተላላፊ ውስጥ ነው፡፡

## የአደጋ ወቅት ስርአቶች አተገባበርና የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ አሰጣጥ

የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ፡-

አንድ ሰው በተለያየ ምክንያት በድንገት ጉዳት ደርሶበት ሲታመም መደበኛውን ህክምና ወደሚያገኝበት የህክምና ተቋም አስኪደርስ ድረስ በቅድሚያ የሚደረግለት እርዳታ ማለት ነው፡፡

አደጋ ያደረሰ አሽከርካሪ ለተሰፋሪዎች የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ለመስጠትና ወደ ሆስፒታል እርዳታመስጠትና ወደ ሆስፒታል የማድረስ ሙያዊ ግዴታ አለበት፡፡

አደጋ በደረሰበት ቦታ ላይ ተጨማሪ አደጋ እንዳይደር ለመከላከል

1. የአደጋ መብራት አብራ
2. አንፀባራቂ ሶስት ጎኖችን ተጠቀም
3. እሳት እንዳይነሳ የሞተር ቁልፍ እጥፋና አውጣ
4. የተሽከርካሪውን ከዋናው መንገድ ወደ ሌላ ለአደጋ ያልተጋለጠ ቦታ መውሰድ ናቸው

በተሽከርካሪ ላይ ሊደርሱ ከሚችሉ አደጋዎች መካከል ተሽከርካሪ ከተሽከርካሪ ጋር መጋጨት፣መገልበጥና በተሽከርካሪ ላይ ከሚነሳ እሳት ሊሆን ይችላል ስለዚህ አሽከርካሪዎች አደጋን ተከላክሎ የተሽከርካሪ ስልት መተግባርና በተሽከርካሪ ላይ እሳት እንዲነሳ ምክንያት ሊሆን የሚችሉ ነገሮች ማወቅ ይጠበቅባቸዋል ፡፡

እነሱም ⟹ በነዳጅ መስመር ላይ የሚፈስ ቦታ መኖር

⟹ የተላላጡና የተዝረከረኩ የኤሌትሪክ መስመሮች

⟹ የሞተር ከመጠን በላይ መሞቅ

⟹ ባትሪ በሚፈታና በሚታደስበት ወቅት የሚኖር የጥንቃቄ ጉድለት

⟹ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ጋን ያለመክደንና በዚያ አካባቢ ሲጋራ ማጨስ ወይም ሌሎች እሳት ሊያስነሱ የሚችሉ ነገሮች መኖርከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ተደርገው መከናወን እንደተጠበቀ ሆኖ አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ የአደጋውን አይነት ሰርቶ ማወቅና ተገቢውን እርዳታ ማከናወን ይኖርብናል ፡፡

## የእሳት አመዳደብና የማጥፊያ መሣሪያዎች

1.የሀ/ ክፍል 1ኛ ደረጃ እሳት ፡- እሳት የሚነሳው ከጠጣር ነገሮች ማለትም ከእንጨት ፣ ወረቀት ፣ጥጥ--- ወዘተ ሲሆን የማጥፊያ መሣሪያው ውሃ ሊሆን ይችላል ፡፡

2. የለ/ ክፍል /2ኛ ደረጃ / እሳት ፡- እሳቱ የሚነሳው ከፈሳሽ ነገሮች ማለትም ቤንዚል ፣ ናፍጣ ፣ ወዘተ ሲሆን የማጥፊያ መሣሪያዎቹም ፎም ፣ ግፊት ያለው ማፈን የማይችል ካፊያ ውሃና ካርቦንዳይ ኦክሳይድናቸው ፡፡

3. የሐ/ ክፍል/3ኛ ደረጃ / እሳት ፡- እሳቱ የሚነሳው ከጋዝ ማለትም ቡቴን ፣ማቴን ወዘተ ከመሣሠሉት ወይም ከኤሌትሪክ ሲሆን የማጥፊያ መሣሪያዎቹ ካርቦንዳይ ኦክሳይድና ድራይፓውደር ናቸው ፡፡

4. የመ/ ክፍል/4ኛ ደረጃ / እሳት እሳቱ የሚነሳው ከብረት ንጥረ ነገሮች ማለትም ፓታሺየም ፣ ማግኒዥየም ከመሣሠሉት ሲሆን የማጥፊያ መሣሪያዎቹም ድራይፓውደር፣ ደረቅ ደቃቅ አሸዋ ናቸው ፡፡

ማሳሰቢያ ፡-

- በ/ለ/ ክፍል እሳት ላይ ካፊያነት ያለው ውሃ መጠቀም እሳቱን ሊያባብሰው ይችላል ፡፡

- በ/ሐ/ እና በ/መ/ ክፍል እሳት ላይ ውሃን እርጥበት ያለውን ነገር መጠቀምበፍፁም የተከለከለ ነው ።
  በአደጋ ምክንያት ብዙ ደም ሲፈስ እስከሞት የሚያደርስ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ በተቻለ መጠን የሚፈሰውን ደም ጥንቃቄ በተሞላበት አኳኋን እንዲቆም መድረግ አስፈላጊነው ።

1. በአደጋ ምክንያት ከተጎዱ ሰዎች ውስጥ ቅድሚያ ደም ለሚፈሰው ተጎጂ እርዳታውን በአፋጣኝ  በመስጠት የሚፈሰውን ደም በማንኛውም ንፁህ ጨርቅ ወይም ፓድ መያዝና ደሙ መፍሰሱ ሊቆም በፋሻ ጠበቅ አድርጎ ማሰር፣
2. የራስ ቅል መድማት ካልሆነ በስተቀር ጉዳተኛውን አስተኝቶ የደማውን የአካል ክፍል ከፋ በማድረግ መደገፍ
3. ጉዳት የደረሰበት ሰው ላይ የጠበቀ የልብስ ቁልፍ ወይም ቀበቶ ካለ ማላላት
4 በውስጥ አካል የመድማት ጉዳት ከደረሰ ተጎጂውን በማንጋለል ማሳረፍና ከሚያስፈልገው በላይ አለማንቀሳቀስ የሰውን መንቀጥቀጥ / ሾክ/ እንዳይፈጥር ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ በአስቸቸኳይ የሀኪም እርዳታ መፈለግ በፍጥነት የህክምና እርዳታ እንዲያገኝ ወደ ህክምና ተቋም መውሰድ ።

በሰውነት ላይ የደረሰበት ስብራት ምልክቶች

1. ስብራት የደረሰበት ሰው ሀይለኛ ህመም ይሰማዋል ፡
2. የተጎዳውን የሰውነት ክፍል ምንቀሳቀስ ያስቸግራል ።
3. ስብራት የደረሰበት የሰውነት ክፍል ቅርፁን ይለውጣል ።
4. እብጠትና አንድ አንዴም የመበለዝ አዝማሚያ ይታያል ።

<u>የስብራት አይነቶችና የሚያስከትሏቸው ጉዳቶች</u>

1. ዝግ ስብስራት ፡- ይህ የብስራት አይነት ከውጪ የመድማት /የመቁሰል /ምልክት አይታይም ።
2. ክፍት ስብራት ፡- ሌላው የስብራት አይነት ሲሆን ከለ ያለው አካል ቁስል የተሰበረው አጥንት ድረስ ዘልቆ ይታያል ። በዚህ ወቅት ጀርሞች ወደ ተሰበረው አጥንትና አካል ክፍል ሊገቡ ስለሚችሉ ጥንቃቄ ያሻል ።

የደም ስሮች ነርቪ ወይም ሌላ ህዋሳቶች በስብራት ሊጎዱ ይችላሉ ።

<u>በሀይለኛ ስብራት ምክንያት የሚደርሱ አደጋዎች</u>

ሀ. በጎድን ስብራት ሳቢያ ልብና ገብት ይጎዳል ፡፡

ለ. በራስ ቅል ስብራት

አደጋን ተሰላክሎ ማሽከርከር

አደጋን ተከላክሎ ለማሽከርከር ለአደጋ መከሰት መንስኤ የሚሆን ጉዳዮችን አስቀድሞ ማወቅና ማስወገድ ቁልፍ የሆነው ተግባር ነው ፡፡

ውጤታ የሆኑ አደጋን ተከላክሎ የማሽከርከር ስልት የሚባሉት ፡-

1. የትራፊክ ፍሰት አካባቢውን በእይታ መቆጣጠር / መከታተል/
2. ሊከሰት የሚችለውን አደጋ መገመት
3. የትራፊክ መብራቶችንና ምልክቶችን ፣ የመንገዱን ሁኔታ ፣ እግረኞችንና ሌሎች ተሽከርካሪዎችን መለየት /
4. ከአደጋ ለማምለጥ የተሽከርካሪን ፍጥነትና ቦታ ለማስተካከል መወሰን /
5. የወሰኑትን ውሳኔ ተግባራዊ ማድረግ ናቸው ፡፡
6. ስለሌላው አሽከርካሪ አላማ እውቀትና ንቃት መገመት ስህተት ነው፡፡ ይህም የአደጋ መንስኤ በመሆኑ

1. ፍሬቻ ካላሳየ አይጠፋም ብሎ መደምደም
   ከፊታቸው መንገድ የሚያቋርጠው ተሽከርካሪ ያዩታል ብሎ ማሳብ
2. የመንገድ ዳር ምልክቶችንና ሌሎች ነገሮችን ያያል ፣ ያከብራል ብሎ መገመት አስቸጋሪና ተገቢ ያልሆኑ ጉዳዮች ናቸው ፡፡
3. ደክመህ ፣ ጭንቀትና ውጥረት ላይ እያለህ እንዲሁም መጠጥ ጠጥተህ ካሽከረከርክ አደጋን መከላከል እንደማትችል ልትገነዘብ ይገባል ፡፡
   ፍጥነት ተቆጣጣጥሮ በማሽከርከር አደጋን ስለመከላከል ፡፡

- ፍጥነት ለመቀነስ ስትፈልግ አስቀድመህ ፍሬን መያዝ አለብህ ምክንያቱም በኃላ የሚመጡ አስቀድመው ማወቅ ስላለባቸው
- አደጋዎች የሚደርሱት እንደ ተሽከርካሪ አብሮ ከሚንቀሳቀሱት ተሽከርካሪዎች ፈጥኖ ወይም ቀስ ብሎ ሲጓዝ ብቻ ነው ፡፡ ስለዚህ የተሻለው አማራጭ ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ጋር የሚስማማ ፍጥነት መጠቀም ነው ፡፡
- ከፍተኛ ፍጥነት የመቆሚያ ርቀትን ያረዝማል ፡፡ በፍጥነት በነዳህ ቁጥር አደጋን ለማስወገድ የሚኖርህ ጊዜ እያነሰ ይሄዳል ፡፡

1. ሌሎች ተሽከርካሪዎች ብዛትና ፍጥነት

2. በመንገዱ ሁኔታ
3. በመንገዱ ዳር በሚኖሩ እግረኞችና
4. በአየሩ ሁኔታ መሆኑን አትዘንጋ

ከአደጋ የማምለጥ ስልት

አደጋን ተከላክሎ የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች ሁል ጊዜ በአደጋ ቢከሰት ሊያመልጡ የሚችሉበት አማራጭ መንገድ አዘጋጅተው ይንቀሳቀሳሉ ፡፡ ስለሆነም በአደገኛ ሁኔታ ላይ አደጋ እንዳይከሰት የሚረዱ ሶስት ነገሮች አሉ እነሱም ፡-

በ

1. መቆም
2. በመሪ ማዞር
3. ፍጥነት መጨመር ናቸው

- ብዙውን ጊዜ ማቆም የተሻለ የአደጋ ማምለጫ አይደለም ነገር ግን ከተጠቀምክ የጎማ እንሽርቶች እንዳይደርሱ ተጠንቀቅ
- በአደጋ ጊዜ ፍሬን ለመያዝና ለማቆም በቂ ርቀት ከሌለ አደጋውን መሪ ተጠቅሞ ተሽከርካሪን በማዞር ማምለጥ የተሻለ አማራጭ ነው ፡፡
- ከጎን ወይም በኃላ ሊገጭህ የሚችል ሲመጣ ከዚህ አደጋ ለማምለጥ የተሽከርካሪህነት ጨምር
- አደጋን ማምለጥ ካልቻልክ እራሱን እንዴት መከላከል እንደምትችል እስከ ዋናው መከላከያ ድህንነት ቀበቶነው ፡፡
- የድህንነት ቀበቶ ሁል ጊዜ በምታሽከረክርበት ወቅት ተጠቀም
- አደጋን ተከትሎ በማሽከርከር ራሳችንና ሌሎችን ከትራፊክ አደጋ እንየብቅ
- አንድም ሰው በትራፊክ አደጋ እንዳይሞት የበኩላችንን አስተዋፅኦ እናበርክት

**ፍጥነት እድሜን እንጂ መንገድን አያሳጥርም !!**